# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 350 ጥር 15


**ወያኔ ታጋዮችን ቢያስር ትግሉን አያስርም። በእጦት ኑሮዓችን በማመሰቃቀል በድህነት ሊያንበረክከን ቢሻም፣ በፍጹም አንበረከክለትም። በተዘረፈ የድሆች ድካም ህንፃዎችን ቢገነቡም የራስ ባልሆነ ጌጥ አንኮራም። የወያኔ የሆነ የኛ አይደለም፤ የእነሱ መከበር የኛ መከበር አይደለም። ወያኔ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዢና ተገዢ፤ በዳይና ተበዳይ፣ ገፊና ተገፊ ናቸው።**

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በደብብ ኦሞ ዞን የተቀሰቀሰው ደም አፋሳሽ ግጭት ተባብሶ መቀጠሉ ታወቀ

ባሳለፍነው ሳምንት በደቡብ ኦሞ ዞን በአመር ወረዳ በሻንቆና ላላ ቀበሌ በጉጅሌው ወያኔ የፌደራል ፖሊሶችና በአካባቢው በሚኖሩ አርብቶ አደሮች መካከል የተቀሰቀሰው ደም አፋሳሽ ግጭት ተባብሶ መቀጠሉን ከስፍራው የደረሰን መረጃ ያሳያል። በእስካሁኑ ግጭት ሻለቃ ለማ አሸናፊ የተባለ የአካባቢው ከፍተኛ የወያኔ ሹምን ጨምሮ ሌሎች 7 የፌደራል ፖሊሶች መገደላቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በአብርቶ አደሮች በኩል የሚኞቹን ቁጥር ለማወቅ ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም። ይሁን እንጅ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ እጅግ የከፋ ጭፍጨፋ በነዋሪዎች ላይ እየፈጸመ እንደሚገኝ ለማወቅ ችለናል። በፋሽስታዊው አገዛዝ የተቆጡት አርብቶ አደሮቹ በግጭቱ የገደሏቸውን የወያኔ ግብረ አበሮች ሬሳ ዋሮ በሚባል ቦታ አከማችተው ለጥቂት ቀናት አንሰጥም ማለታቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በመጨረሻ በአካባቢው ሽማግሌዎች አደራዳሪነት ሬሳዎቹ ሊሰጡ መቻላቸው ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በአርብቶ አደሮቹ እየደረሰበት ባለው መራር ሽንፈት ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ የገባው እብሪተኛው ወያኔ ባሳለፍነው ሳምንት ተጨማሪ ልዩ የአጋዚ ጦር ወደ ቦታው በመላክ የዘር ማጥፋት ወንጀል እየፈጸመ እንደሚገኝ ያደረሱን ምንጮቻችን የአካባቢው ነዋሪዎች የድረሱልን ጥሪ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማቅረባቸውን ለማወቅ ችለናል። የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በአካባቢው እየፈጸ የሚገኘውን የዘር ማጥፋት ወንጀል በተመለከተ ለማነጋገር የአካባቢው የወያኔ ቱባ ሹም ወደ ሆነው እምነት የተባለ ግለሰብ በተደጋጋሚ በስልክ ለማግኘት ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም። ግለሰቡ የስልክ ጥሪያችንን ቢመልስም፤ ለማነጋገር ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል። በአካባቢው አሁንም ድረስ የተኩስ እሩምታና አልፎ አልፎ ደግሞ የከባድ መሳሪያ ድምጽ እንደሚሰማ የአካባቢው ምንጮቻችን ያደረሱን መረጃ ያመለክታል።

## በደቡብ ወሎ ዞን አንድ ወጣት በአሰቃቂ ሁኔታ በጥይት ተደብድቦ ተገደለ

በደቡብ ወሎ ዞን ደጋን ቀበሌ ነዋሪ የሆነ አንድ ወጣት ባሳለፍነው ቅዳሜ ምሽት በአካባቢው የፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ሚሊሻዎች ከ 30 በላይ በሆነ ጥይት ተደብድቦ በአሰቃቂ ሁኔታ መገደሉን ለማወቅ ተችሏል። የፋሺስቱ ወያኔ አገዛዝ በአካባቢው የሚፈጽማቸውን የተለያዩ ጭቆናዎች፤ በደሎችና ግፎች በግንባር ቀደምትነት በመቃወምና በማወገዝ ይታወቅ የነበረው ይህ ወጣት ከድርጊቱ እንዲታቀብ በአገዛዙ ሚሊሻዎች በተደጋጋሚ ታስሮ ከመፈታቱም በላይ ለበርካታ ጊዜ የተለያዩ ማስፈራሪያዎችና ዛቻዎች ይደርሱት እንደነበር ታውቋል። ይሁን እንጂ ወጣቱ በወያኔ ቅጥረኞች ለሚደርሱት ዛቻና ማስፈራሪያዎች ቁብ ሳይሰጥ በቀበሌው ከፍተኛ የፖለቲካ መነቃቃትን በመፍጠር ነዋሪው ለመብቱ እንዲነሳ በስፋት ይቀሰቅስ የነበረ ሲሆን ይህ የህዝብ ልጅ በቀበሌው ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነትንና ከበሬታን አትርፎ እንደነበርም ለማወቅ ችለናል። የወጣቱ መገደል የቀበሌውን ነዋሪዎች ከፍተኛ ሐዘን ውስጥ ከቷቸው እንደሚገኝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ጥቂት የማይባሉ የወጣት የቅርብ ወዳጆች በጅምላ ወደ እስር መጋዛቸው ታውቋል። እብሪተኛው ወያኔ ምናልባትም በጅምላ ለእስር በተዳረጓት የሟች የቅርብ ወዳጆች ላይ ተመሳሳይ የግድያ እርምጃ ሊወስድ ይችላል በሚል ከፍተኛ ስጋት በነዋሪዎች ዘንድ አንዣቦ እንደሚገኝ ለማወቅ ችለናል።

በሌላ ዜና በዚያው በደ. ወሎ ዞን ነዋሪዎች ላይ የተለያዩ የግፍ በደሎችንና የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በመፈጸምና፤ ትዕዛዝ በማውረድ በማስፈጸም የሚታወቀው የዞኑ የደህንነት ቢሮ ሃላፊ የሆነው ፍትሃዊ ግደይ የተባለ የወያኔ ቅጥረኛ በአማራ ወጣቶች የጋራ ንቅናቄ (አወጋን) ልዩ ሐይል በጥይት ተደብድቦ መገደሉን ለማወቅ ችለናል። የወያኔ ተላላኪ የነበረው ሟች ፍትሃዊ ግደይ የአይኑ ቀለም ያላማረው ማንኛውንም የዞኑ ነዋሪ ያስገድል፤ ያሳስርና፤ ያስደበድብ እንደነበር ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ከግለሰቡ ጋር በመሆን በነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ በደሎችንና ወንጀሎችን ይፈጽሙ፤ ..... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## በኢትዮጵያ ወደ ከፋ ድህነት የገቡ ዜጎች ቁጥር በእጅጉ መጨመሩን የአለም ባንክ ጥናት አጋለጠ

በዘራፊው የወያኔ አገዛዝ የተሳሳቱ ፓሊሶዎችና የአገዛዙ ቱባ ሹማምንት በሚፈጸሙት የከፋ ሙስና ሳቢያ በኢትዮጵያ ባለፉት አሥር ዓመታት በአስከፊ ድህነት ውስጥ ይገኙ የነበሩ ዜጎች ወደ ተባባሰ የድህነት አረንቋ መውረዳችውን የአለም ባንክ ጥናት አጋለጠ። በጥናቱ እንደተመለከተው በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ እጅግ አስከፊ በሆነ የድህነት አረቋ ውስጥ ተዘፍቆ በከፋ ስቃይ የዕለት ኑሮውን የሚገፋው ሕዝብ ቁጥር ከ 25 ሚሊዮን በላይ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ2005 በአገሪቱ ከነበሩት ድሆች ይልቅ እ.ኤ.አ. በ2011 የነበሩት ድሆች የበለጠ መደህየታቸው ተመልክቷል። እጅግ ዝቅተኛ በሆነ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ደሃ ቤተሰቦች እ.ኤ.አ. ከ2005 ጀምሮ የኑሮ መሻሻል አለማሳየታቸውን ያጋለጠው ሪፖርቱ እንዲያውም አንዳንዶቹ በፊት ከነበሩበት የድህነት ሁኔታ ወደ ተባባሰ ድህነት መውረዳቸው በጥናቱ ተገልጿል። በጥናቱ መሠረት እ.ኤ.አ. በ2005 የነበሩት የአገሪቱ ድሆች መጠን እ.ኤ.አ. በ2011 ከነበሩት ድሆች ገቢ መጠን ጋር ሲነፃፀር፣ በ2011 የነበሩት ድሆች በ2005 ከነበሩት ያነሰ የገቢ መጠን እንደነበራቸው ሪፓርቱ አጋልጧል። በመሆኑም እስከ 2011 በነበሩት ስድስት ዓመታት ውስጥ ድሆች የነበሩ ሰዎች ወደባሰ ድህነት ውስጥ ለመግባት ተገደዋል።

ከዚህ ባሻገር በንፅፅር የተሻለ የተባለ ኑሮ ያላቸው ሰዎችም እ.ኤ.አ. ከ2005 ጀምሮ በነበሩት ስድስት ዓመታት ውስጥ ከነበሩበት የኑሮ ደረጃ መንሸራተታቸው ተመልክቷል። በተለይ በከተሞች አካባቢ ይህ ክስተት ተንሰራፍቶ እንደታየ የአለም ባንክ ጥናት ያትታል። በአገሪቱ ከሚገኙት ክልሎች ውስጥ እ.ኤ.አ. ከ2005 በፊት ከሌሎች ክልልሎች በንጽጽር በደህና ደረጃ ይገኙ ከነበሩት መካከል እንደ ሶማሌና አፋር ያሉት ክልሎች እ.ኤ.አ. በ2011 ወደ ተባባሰ የድህነት ቀጣና መውረዳቸውም በጥናቱ ታይቷል። ከዚህ ባሻገር በአዲስ አበባና በድሬዳዋ የሚታየው የድሆችና የሥራ አጦች ቁጥር ከ 27 በመቶ እንደሚበልጥ ይፋ ተደርጓል። ..... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## "ቃሊቲ ውስጥ የታሰሩ ንጹኋን ዜጎች ስቃይ አሁንም ከፊቴ አሉ" ስዊድናዊዉ ጋዜጠኛ ማርቲን ሺብ

ለአንድ ዓመት ከሁለት ወር ከሥራ ባልደረባው ዮሐን ፔርሶን ጋር በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ለእስር ተዳርጎ የነበረው ጋዜጠኛ ማርቲን ሺብዬ በማዕከላዊ እስር ቤት ውስጥ ቶርቸር (አካላዊ ስቃይ) የሚፈጸምባቸው ጩኸታቸው ይሰማኛል። የቃሊቲ ማጎሪያ ውስጥ የታሰሩ ተማሪዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ፖለቲከኞች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ ንጹሃን ዜጎች፣ ስቃይ አሁንም ከፊቴ አለ፤ የሚሞቱት ሰዎች ሊረሱኝ አይችሉም፤ የእስር ቤቱ ጠረንና ሽታ ይከተለኛል፤ በአካል ደህና ብመስልም አእምሮዬ ግን አሁን ድረስ ሰላም የለውም" በማለት በእስር ቤት ስለተመለከተው አስቃቂ ግፎችና ግድያዎች ተናገረ።

"በአካል ሰላም አለኝ፤ አእምሮዬ ግን አልዳነም፤ ሁሌም እረበሻለሁ፤ በዓይኔ ያየኋቸው፣ በጆሮዬ የሰማኋቸውና በበቂ ምስክሮች ያረጋገጥኳቸው ሁኔታዎች ዕረፍት ይነሱኛል" ሲል አስተያየቱን የጀመረው .... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ዩሲዉድኑ ኤች ኤንድ ኤም ከደቡብ ኦሞ ስምጥ ሸለቆ የሚበቅል የጥጥ ምርት እንደማይገዛ አሳወቀ

የጉጅሌው ወያኔ ሹማምንት ከሼህ ሙሃመድ አላሙዲን ጋር በመሻረክ በኦሞ ስምጥ ሸለቆ አካባቢ የሚኖሩ በብዙ አስር ሺዎች የሚገመቱ ነዋሪዎችን የሰብአዊ መብታቸውን በመጣስ በግፍ በማፈናቀል ቦታውን ለጥጥ እርሻ ማዋላቸውን ተከትሎ ከፍተኛ ተቃውሞ በኢትዮጵያውያንና በአለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች መቅረቡ የሚታወስ ሲሆን ተቃውሞዎችን ተከትሎ ከአካባቢው ከሚበቅለውን ጥጥ ከፍተኛውን ምርት ይረከብ የነበረው ቸ ኤንድ ኤም የተሰኘው የአውሮፓ ግዙፍ ኩባንያ ምርቱን አልቀበልም ሲል አሳውቋል። ድርጅቱ በመግለጫው እንዳስታወቀው ነዋሪዎችን ከመኖሪያ ቦታችው ማፈናቀል በአለማቀፍ ህግ መሰረት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት ወንጀል መሆኑን በመጠቆም በኦሞ ስምጥ ሸለቆ የጥጥ ምርቱ ይህንን አለማቀፍ ህግ በመጣስ ስለሚመረት ላለመግዛት መወሰኑን አስታውቋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ከአካባቢው የሚመረት ጥጥ ለድርጅቱ ማቅረብ እንደማይችሉ ከአቅራቢዎች ጋር የውል ስምምነት የተፈራረመው ቸ ኤንድ ኤም አቅራቢዎች ይህን ህግ ጥሰው ቢገኙ ከኢትዮጵያ የጥጥ መርት መረከብ እንደሚያቆም ተገልጿል።

## ጊዜው የሕዝባዊ እምቢተኝነት ነው!!!

(ከዚ ህ በፊት ወጥቶ የነበር የግንቦት 7 ርዕሰ አንቀጽ)

በአሁኑ ወቅት በአገራችን በከተሞችና በገጠሮች እየታዩ ያሉ ምልክቶችን በጥንቃቄ የመረመረ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መታዘቡ አይቀርም።

በአንድ በኩል፣ ወያኔ የተወገደባት፣ ፍትህ የሰፈነባትና የበለፀገች ኢትዮጵያ እውን ሆና የማየት ተስፋችን እየለመለመ ነው። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ዉስጥ ለረጂም ዓመታት በሕዝብ ላይ ሰፍኖ የነበረው የፍርሀት ደመና እየገለጠ በመሆኑ ተዘግተው የቆዩ አንደበቶች መናገርና "ይኸ ሁሉ ግፍ ለምን?" ብለው መጠየቅ ጀምረዋል። ይህንን መነቃቃት በአስተሳሰብም፣ በተግባርም፣ በኪነጥበብም እያየነው ነው። የኢትዮጵያ ወጣቶች ለውጥ በአገራችን ሊመጣ እንደሚችል ከማመን አልፎ ራሳቸውን በለውጥ አምጭ ኃይልነት መመልከት ጀምረዋል። በርካታ ወጣቶች ወያኔን በትጥቅ ለመገዳደር የወሰኑ ወገኖቻችንን እየተቀላቀሉ በዚህም ምክንያት ጉልበታቸውን እያፈረጠሙ ነው። የለውጡ እርሾ ከሲቪሉ አልፎ በመከላከያ ሠራዊቱ እና በኢሕአዴግ ድርጅቶች ውስጥም እየተብሰለሰለ ነው። የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት፣ ህወሓት ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚጠቀምበት ኃይል መሆኑ እያበቃ በአንፃሩ የትግሉ አጋር የሚሆንባቸው ሁኔታዎች እየታዩ ነው። በሁሉም የሠራዊቱ ክፍሎች ጉምጉምታው ወደ ጨኸት እየተቀየረ በመሆኑ ሠራዊቱ በአለቆቹ ላይ የሚነሳበት ጊዜ እሩቅ አይደለም። በተለያዩ ምክንያቶች ህወሓትን ወይም ህወሓት የፈጠራቸውን ድርጅቶች የተጠጉ በአጠቃላይ ኢሕአዴግ በሚባለው ስብስብ ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችንም "ለመሆኑ ማንን ነው እያገለገልን ያለነው?" ብለው በመጠየቅ ላይ ናቸው። በዚህም ምክንያት ወያኔ ውስጡ እየተረበሸ ነው። ከኢትዮጵያም ውጭ በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያለው ቁጣና ዝግጁነት ከወትሮው እጅግ የላቀ ነው። በአጭሩ፣ በሁሉም አቅጣጫ፣ ደረጃ በደረጃ የሕዝባዊ እምቢተኝነት እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል።

በአንፃሩ ደግሞ፣ የጨለማ ንጉሥ የሆነው ወያኔ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብን ወደ ፍርሀት ቆፈን ለመመለስ እስሩን ከመቸውም በላይ ያጧጧፈበት ጊዜ ነው። በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በአፋር በሶማሊ ... በመላው ኢትዮጵያ ብሩህ ራዕይ የሰነቁ ወጣቶችና አዛውንት ታድነው እየታሰሩ ናቸው። የወያኔ እስር ቤቶች በአርቆ አስተዋይ ዜጎቻችን ተሞልተዋል። ወትሮም ከፍተኛ የነበረው ስደት ብሶበታል፤ ለእውነት በጽናት የቆሙ ጋዜጠኞች ወይ ታስረው፣ አልያም ተሰደው አልቀዋል። የወያኔ የግዴታ ስልጠና አገሩን እያመሰው ነው። የኢትዮጵያዊያን ኑሮ በእጦቶች የታጀበ ሆኗል። የነፃነት እጦት፣ የፍትህ እጦት፣ የመብራት እጦት፣ የስኳር እጦት፣ የዘይት እጦት፣ የታክሲ እጦት፣ የመኖሪያ ቤት እጦት፣ እጦት፣ .... እጦት።

እነዚህ ሁለት ተፃራሪ እውነታዎች ሁለት ተፃራሪ ኃይሎች ለወሳኝ ፍልሚያ ፊት ለፊት መፋጠጣቸዉን በግልጽ ያሳያሉ። ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃነትና ባርነት፣ ፍትህና ጭቆና፣ ደስታና ሀዘን፣ ተስፋና ተስፋ መቁረጥ፣ ብልጽግናና ድህነት፣ እውቀትና ድንቁርና፣ ብርሃንና ጨለማ፣ ለወሳኝ ግጥሚያ ተፋጠዋል። ይህ ፍጥጫ የኢትዮጵያን የወደፊት እጣ ፈንታን በመወሰን ረገድ አቢይ ሚና የሚኖረው ወሳኙ ግጥሚያ – ሕዝባዊ እምቢተኝነት – መጀመሩን አብሳሪ ነው። የነፃነት፣ የፍትህ፣ የተስፋ፣ የብልጽግና፣ የእውቀትና የብርሃን ወገኖች ነን የምንል ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ይህንን ፍልሚያ በድል መወጣት ግዴታችን ነው።

ወያኔ ታጋዮችን ቢያስር ትግሉን አያስርም። በእጦት ኑሮዓችን በማመሰቃቀል በድህነት ሊያንበረክከን ቢሻም፣ በፍጹም አንበረከክለትም። በተዘረፈ የድሆች ድካም ህንፃዎችን ቢገነቡም የራስ ባልሆነ ጌጥ አንኮራም። የወያኔ የሆነ የኛ አይደለም፤ የእነሱ መክበር የኛ መክበር አይደለም። ወያኔ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዢና ተገዢ፤ በዳይና ተበዳይ፣ ገፊና ተገፊ ናቸው።

ተበዳይና ተገፊ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘረኞች፣ ሙሰኞችና ከፋፋዮች የህወሓት ባለሥልጣኖቻቸውና ሎሌዎቻቸው ላይ ይነሳሉ። የተጀመረው ሕዝባዊ እምቢተኝነት አመቺ በሆኑ መንገዶች ሁሉ ይጧጧፋል።

የወያኔ ትዕዛዛትን መሻር፤ በሥራ ላይ መለገም፤ ግብር አለመክፈል፤ አድማ መምታት፤ የወያኔ ካድሬዎችን ማግለልና ማዋረድ፤ የነፃነት ኃይሎችን መደገፍ፤ የፓሊስና የጦር ሠራዊት አባላትን ማቅረብ እና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እነሱም የትግሉ አካል እንዲሆኑ ማበረታታት፤ ህሊና ያላቸው የኢሕአዴግ አባላት የሕዝቡን ትግል እንዲያግዙ ማበረታታት ... – እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ የትግል ስልቶች ከአሁን ጀምሮ በተከታታይ በሥራ ላይ መዋል ይኖርባቸዋል። የወያኔን የጭቆና ምሽግ ከውስጥ መሸርሸር፤ ከውጭ መደርመስ ይኖርበታል። የመሸርሸርና የመደርመስ ሥራዎች ተደጋግፈው እንዲሄዱ ማድረግ ይገባል። ጊዜው የእምቢተኝነት ነው።

አርበኞች ግንቦት 7: ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ሕዝብ አጠገቡ ባሉት መሪዎቹ አስተባባሪነት በአንድነት እንዲነሳ ጥሪ ያቀርባል፤ በመላው ዓለም ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገው ሁለገብ ትግል በጽናት እንዲደግፉ ያሳስባል። ይህንን ትግል በድል መወጣት ግዴታችን ነው፤ እንወጣዋለንም !

## ስዊድን ዉስጥ የወያኔዋ አምባሳደር ኢትዮጲያውያን ላይ የመሰረተችዉ ክስ ውድቅ ሆነ

ቀደም ሲል የኢህአዴግ መንግስት ፤ በስዊድን-ስቶኮሆልም አዘጋጅቶት የነበረው የቦንድ ሽያጭ ዝግጅት ላይ ኢትዮጲያውያን ከፍተኛ ተቃውሞ ማሰማታቸው ይታወቃል።" ከአባይ በፊት ዘረኝነት ይገደብ" በሚል መርህ ተቃውሞውን ያደረጉት ኢትዮጲያውያን፤ ዜጎች ያለፍርድ እየታሰሩና እየተገደሉ ባለበት ሁኔታ ገንዘብ ለመሰብሰብ መሯሯጥ፤ በሀገርና በህዝብ ላይ መቀለድ እንደሆነ በመናገር ነበር- ተቃውሟቸውን ጫማና እንቁላል በመወርወር የገለጹት።

ኢትዮጲያውያኑ አምባሳደሯን መኪና ላይ የእንቁላል መዓት በመወርወር ተቃውሟቸውን ሲገልጹ፤ አምባሳደር ወይንሸት ከመኪናቸው መውጣት ተስኗቸው ተስተውለዋል። በኦትዮጲያውያኑ ጫማና እንቁላል የተወረወረባቸው በስዊድን የኢትዮጲያ አምባሳደር ወይንሸት ታደሰ፤ "ስራዬን መስራት እስከማልችል ድረስ በደል ደርሶብኛል" በማለት ለስዊድን ፖሊስ ክስ ይመሰርታሉ።የአምባሰደሯን ክስ ተከትሎ የስዊድን ፖሊስ ባቀረበላቸው ጥሪ መሰረት ቃል ለመስጠት የሄዱት የኢትዮ-ስዊድን ግብረ-ሀይል አስተባባሪ አክቲቪስት መቅደስ ወርቁ እና የኢትዮጲያ ዲሞክራቲክ መድረክ ምክትል ሊቀ-መንበር አቶ ሞላ፤ ኢትዮጲያ ውስጥ ስላለው የሙብት ረገጣና በስፋት ለስዊድን ፖሊስ በማብራራት፤ ተቃውሞው የተደረገው የሰብዓዊ መብት ጥሰትን፣ዘረኝነትን እና ሙስናን ለመቃወም እንደሆነ አስረድተዋል።

ጉዳዩን የተመለከተው የስዊድን ፖሊስም በስዊድን ህግ መሰረት የዚህ ዓይነት ተቃውሞ ማድረግ መብት እንጂ ወንጀል እንዳልሆነ በመጥቀስ እና ክሱ ውደ ፍርድ ቤት የሚያመራበት አንዳችም የህግ ምክንያት እንደሌለ በማብራራት የአምባሰደሯን ክስ ውድቅ እንዳደረገው አክቲቪስት መቅደስ ተናግረዋል። የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትር አቶ ሬድዋን ሁሴን ከወራት በፊት በዋሽንግተን ዲሲ የልብስ መደብር ውስጥተቃውሞ ባቀረቡባቸው አክቲቪስቶች ላይ የመሰረቱት ክስ ሰሞኑን በአሜሪካ ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ ይታወቃል።

## በደቡብ ወሎ ዞን አንድ ወጣት በአሰቃቂ ሁኔታ

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

በተባባሪነት ያስፈጽሙ የነበሩ የአገዛዙ ቅጥረኞ ቀጣይ የጥቃቱ ኢላማ ልንሆን እንችላለን በሚል ከፍተኛ ስጋት ውስጥ መውደቃቸው ታውቋል። ፍትሃዊ ግደይ የፋሽስቱ ወያኔን የከፋፍለህ ግዛ ስትራቴጂ በዞኑ ለመተግበር የተለያዩ እኩይ ሴራዎችን በመጎንጎንና በማስፈጸም ይታወቁ እንደነበርም ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ከነዚህም መካከል በዞኑ ለዘመናት ተቻችለው በመከባበርና በመፈቃቀር የሚኖሩትን ሁለቱ ታላላቅ ሐይማኖች የእስልምናና የክርስትና ሐይማኖቶች በመካከላቸው ቁርሾን ለመፍጠር ሙስሊሙን ጽንፈኛ በማለት ይፈርጅ እንደነበርና፤ ክርስቲያኑን ደግሞ የድሮ ስርአት ናፋቂ በማለት በሐማኖቶቹ መካከል የጥላቻ መርዙን ይረጭ እንደነበር ለማወቅ ችለናል። ግለሰቡ ከተገደለ በኋላ በዞኑ ከፍተኛ ውጥረት የነገሰ ሲሆን በተለይ በወራኢሉ ከተማ ከፍተኛ ፍተሻ መኖሩን ከስፍራው የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

## በኢትዮጵያ ወደ ከፋ ድህነት የገቡ ዜጎች ቁጥር

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአለም ባንክ ሪፖርት ዘራፊው የወያኔ አገዛዝ አገራችንን እና ህዝባችንን ተብትቦ የስንግ የያዘውን ድህነት በተመለከተ እንዳሻው በሚፈነጭበት ቴሌቪዥን ከሚደሰኩረው ቀቢጸ ተስፋ ጋር ፈጽሞ የሚቃረን ሲሆን በሙስና የነተቡት የወያኔ ቱባ ሹማምንቶች እንደተለመደው ሪፓርቱን ለማስተባበል ላይ ታች እየማሰኑ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። ይሁን እንጂ ላለፉት 24 የጨለማ አመታት የአገር ሐብት በመዝረፍ ህዝቡን በጠኔ ተብትበው ሲጫዎቱበትና ሲያላግጡበት የኖሩት ቱባ ሹማምንቱ ሪፖርቱን በተመለከተ የሚያቀርቡት በውሸት የታጨቀ ማስተባበያ ፈጽሞ ሰሚ ሊያገኙ እንደማይችሉ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በስፋት እየተነገረ እንደሚገኝ ዘጋቢያችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል።

## ሬድዋን ሁሴንና የወደቀው ክሱ !

በኢትዮጵያችን ህግ ትርጉሟን አጥታ፤ፍትህም ተዋርዳ ከተጣለች የህወሃትን እድሜ ብታስቆጥርም እነርሱ ግን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ስለ ህግ የበላይነት ማውራታቸውን አላቆሙም። እነዚህ ቡድኖች የህግ የበላይነት ሲሉ እነርሱ ከፍ ብለው ከህግ በላይ፤ ከእነርሱ መንደር ያለሆነው ደግሞ ዝቅ ብሎ ከሥር ከጫማቸው ሥር ሁኖ እነርሱን ተሸክሞ የሚኖርበትን ሥርዓት ማስጠበቅ የሚችለውን ህግ ነው። እናንተን መሸከም ከበደኝ፤ ቀንበራችሁ ሰበረኝ የሚል ሰው ከተገኘ የሚጠብቀው ፍርድ "አሸባሪነት" ነው። ይህ የከፉዎችና የልበ ደንዳኖች ፍርድ ፍትህ ተብሎ በህወህቶች መንደር ይወደሳል። መፅሃፍ እንዲህ ይላል "ከፍዎች ሰዎች ፍርድን አያስተውሉም"። ህወሃቶች ባወጧቸው ህጎች የስንት ንፁሃን ዜጎች ቤት እንደፈረሰ፤ ስንት ህፃናት አሳዳጊ አልባ እንደሆኑ፤ ስንቶች አገራችውን ትተው ተሰደው እንደጠፉ ቆጥረን አንዘልቀውም። በህወሃት መንደር ህግ ዜጎችን ማጥቂያ እና ማስጨነቂያ መሣሪያ እንጂ የፍትህ ማስከበሪያ መሳሪያ አይደለም። በህወሃት ህግ ብዙ ዜጎች ጠፍተዋል፤ ብዙዎች ደግሞ በብዙ ጭንቀት እና መከራ ውስጥ ይገኛሉ።

በህወሃት መንደር የተሰባሰቡ ግለሰቦች እንደምን ያለ ብርቱ ጭለማ እና ድንቁርና ውስጥ እንደሚገኙ በርካታ ምሳሌዎችን ማንሳት እንችላለን። ለአሁን ግን ማሰብ ካቆሙ ቅጥረኞች መካከል ሬድዋን ሁሴን የተባለው ግለሰብ የሆነውን እንመልከት። ሬድዋን ሁሴን፤ ጌቶቹ እና ሌሎች መሰሎቹ ያሉበትን ዘመን ረስተው ወይም መረዳት ተስኗቸው፤ ከስልጣኔ መንገድም ወጥተው እንዲሁ በጭለማ ዓለም እየተደናበሩ ይገኛሉ። ሬድዋን ሁሴን ያለበትን ዘመንና የያዘው የህዝብ ስልጣን የሚያስከትልበትን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት መገንዘብ ስለተሳነው ቀና ብሎ ተናገረኝ ባላው ወጣት ላይ በአሜሪካን አገር ክስ መመሥረቱን ስንሰማ በብርቱ ተደንቀናል። አገራችንም በእንደነዚህ ዓይነት ማስተዋል በጎደላቸው ግለሰቦች የምትመራ መሆኑም በእጅጉ ያሳዝነናል።

ሬድዋን ሁሴንን በቨርጂኒያ አገረ ግዛት ያገኘው ወጣት ህወሃቶች በወገኖቹ ላይ የጫኑባቸው ሸክም ያሳመመው፤ በዚህም ህመም የተቆጣ ቁጣውንም በሰላም የመግለፅ መብቱ ያለ ገደብ የተከበረባት አገር ውስጥ ኗሪ ነው። ሬዲዋን ሁሴንን የመሰለ ራሱን ለምናምንቴ ነገር አሳልፎ የሸጠ ትንሽ ግለሰብ ይቅርና የሃያሏ አገር አሜሪካን ፕሬዝዳንትም ብዙ ወቀሳና ስድብ ይደርስበታል።ፕሬዝዳንቱም የህዝብ ተቀጣሪ መሆኑን ስለሚያውቅ ተወቀስኩ ወይም አንድ ዜጋ ተናገረኝ ብሎ የበቀል ሰይፉን አይመዝም። ፕሬዝዳንቱ ተሰደብኩ ብሎ ክፉ ቢናገር የሚከተለው መዘዝ ከስድቡ የበለጠ ጉዳት ስለሚያደርስበት ስድቡን መቻል እና መሸከም የሥራው አንዱ አካል ይሆናል።ህግ ባለበት አገር የአገሩ መሪ ህዝቡን ፈርቶ ይኖራል እንጂ፤ ህዝብ መሪውን ፈርቶ አይኖርም። ሬዲዋንና መሰሎቹ ግን እንዲህ አይደሉም። ህዝብን ረግጠውና አስፈራርተው መኖር የጎበዝ ተግባር ነው ብለው አምነው ተቀብለዋል።

ህወሃት ትንሹንም ትልቁንም ፈርቶ፤ ፍርሃቱ በወለደው ጭካኔ ዜጎችን ሁሉ አስሮ መኖር ልማዱ ሁኗል። በኢትዮጵያ ዜጎች ህወሃቶችን ፈርተው፤ ህወሃቶችም ዜጎችን አስፈራርተው የሚኖሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይሄ ሁኔታ ለማንም ወይም ለምንም እንደማይበጅ ለህወሃቶች ብንነግራቸውም ልቦናቸው በትዕቢት ታውሯልና አይሰሙንም። ሬድዋን ሁሴንም የዚህ መራራ ትዕቢት ትሩፋት ነው። እንደምን ሁኖ ቀና ብለው ያዩኛል፤ እንደምንስ ሁኖ ይናገሩኛል፤ እንደምንስ ሁኖ ስሜ በገበያ መሃል ይነሳል የሚል ትዕቢት ስለተፀናወተው ክስ መሠረተ፤ ክሱ ግን በህግ ፊት ሚዛን የማይደፋ በመሆኑ በአቃቤ ህጉ ውድቅ ተደረገ። ሬዲዋንም የፍትህን መራራ ፅዋ ተጎንጭቶ ሊውጣት ግድ ሆነበት። የህወሃት ቅጥረኞችና ህወሃቶች ውድቅ ከሆነው ከሬድዋን ህሴን ክስ ልትማሩ የሚገባችሁ የህግ የበላይነት በሰፈነበት አገር እናንተ ከተራው ዜጎች እኩል እንጂ የበላይ ልትሆኑ እንደማትችሉ፤ ከመጋረጃው ጀርባ ሁናችሁ ፍትህን የምትጠመዝዙበት እጃችሁ እንደሚታሰር እና ገና ወደፊት ደግሞ የእጃችሁን እንደምታገኙ ነው። እናንተን ከተራው ዜጋ እኩል የሚያደርግ ህግ ሲፈጠር የታጠቃችሁት ጠብመንጃ የሸንበቆ ምርኩዝ፤ የመኖሪያ ድንኳን የሆናችሁ ማን አለብኝነታችሁ ደግሞ ፀሃይ እንዳየው ጤዛ እንደሚተን ልብ ልትሉ ይገባል። ሬዲዋንን የተናገረው ወጣት ኢትዮጵያ ውስጥ ሁኖ ቢሆን ኑሮ ዛሬ እነሬዳዋን ፈተው በሚለቋቸው ውሾች ሊደርስበት የሚችለውን ስቃይ ስናስበው ይዘገንነናል። ከባህር ማዶ መሆኑ ከሥጋዊ ስቃይ አድኖታል።

እንግዲህ ህወሃቶች የምትፈፅሟቸው ግፎች በየደረሳችሁበት እየተከታተሉ እረፍት ማሳጣታቸውን የሚያቆሙ አይሆንም። የምትሠሯቸው ግፎች የሚያሳድዱት እናንተን ብቻ አይደለም። ከእናንተ አብራክ የሚፈጠሩ ልጆቻችሁንም ጭምር የከፉ ሥራዎቻችሁ ሰለባዎች ከመሆን አያመልጡም። ልጆቻችሁ ተሳቀው ከህዝብ ዓይንና ጆሮ ተደብቀው መኖር ዕድል ፈንታቸው ይሆናል። እናንተ የምትፈፅሙት ወንጀል ለልጆቻችሁ ኩራት ሳይሆን እፍረት፤ ክብር ሳይሆን ውረደት ሁኖ ይቆያቸዋል። ቢያንስ ለልጆቻችሁ ሠላም ስትሉ ከእኩይ ድርጊታችሁ መታቀብ ይሻላችሁ ነበር። እናንተ ግን ለትውልዱ ሠላም የሚሻለውን ትታችሁ የጥፋቱንና የደም መፋሰሱን መንገድ መርጣችኋልና ወዮታ አለባችሁ።

እናንተን መታገል ከስጋና ከደም ጋር የሚደረግ ትግል ብቻ አይደለም። የምትፈፅሟቸው ግፎች ከሰው ልጅ አዕምሮ የሚፈልቁ ብቻ አይመስልም።ከእናንተ ጋር የሚሰራ ሌላ የማይታይ የክፋት አባት ያለ እስከሚመስለን ድረስ ግፋችሁ አንገፍግፎናል። ይህን ግፍ ዝም ብለን የምናይ አይመሰላችሁ። ሊከፈል የሚገባውን መሥዋዕትነት ለመክፈል ተዘጋጅተናል። ወጣቶችም ሳያቅማሙ አያቶቻቸው በተመላለሱባቸው ኮረብቶች ላይ ተሰማርተዋል። ክፉውን ለመቃወም፤ ደም አፍሳሹን ለማስቆም፤ ሌባውን ተው ለማለት፤ ትዕቢተኛውን አደብ ለማስያዝ፤ የነፃነት ቀበኛውን ለማስተማር ሰይፋቸው ከአፎቱ ተስማምቶ ተዘጋጅቷል።

የተከበራችሁ ያገራችን ዜጎች ሆይ !

ህወሃቶች በዜጎችቻን ላይ የሚፈፅሙትን ግፍ ለእናንተ መንገር ለቀባሪው እንደ ማርዳት ይሆንብናል። የእነዚህ ቡድኖች ግፍ ፅዋውን ሞልቶ እየፈሰሰ ነው።የአገሪቷን ታሪክ አንድ በአንድ ለማጥፋት እየሠሩ ይገኛሉ-በየቦታው በእሳት የሚቃጠሉት ታሪካዊ አምባዎቻችን የአገሪቷን ታሪክ የማጥፋት ዘመቻ አካል ነው።ዜጎች አገር አልባ እንዲሆኑ ተደርገዋል፤ አብሮ በኖረው ህዝብ መካከል የሚዘራው የጥላቻ ዘር ለአገራችን አደጋ ሁኖ ተደንቅሯል። አገራችን ታሪኳ በሚመሰክርላት ሥፍራ ላይ እንዳትሆን፤ ለአፍሪካ ቀንድም ሆነ በአጠቃላይ ለዓለም ሠላም መጫወት የሚግባትን ሚና እንዳታከናውን ተደርጋለች። በተቃራኒው የግጭት አምባ፤ የችጋር ምሳሌ፤ የስደት ምልክት ሁና ከውዳቂ መንግስታት ተርታ ገብታለች። ይሄ ሁሉ እርግማን በህወሃት ምክንያት የመጣ ነው።

እኛ በአገራችን ላይ የተተከለውን ህወሃት የተባለውን እርግማን ነቅለን ለመጣል የምንችለውን ሁሉ እያደረገን ነው። ህወሃቶች የነፃነትን ዋጋ ተረድተው፤ ለፍትህ ክብር ሰጥተው፤ ዜጎችን አክብረው፤እኛም ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር እኩል ነን። ከማንም አንበልጥም፤ ሌላውም ከእኛ አያንስም ብለው በሰለጠነ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ ለመወያየት ፍርሃታቸው እና ድንቁርናቸው ቢፈቅድላቸው ለሁላችንም መልካም ነበር። ይህ መልካም ነገር ግን የእኛ ምኞት ብቻ ሁኖ ቀርቷል።ህወሃቶች የተፀናወታቸው ትዕቢት የሰይጣን ትዕቢት ስለሆነ እንዲሁ በቀላሉ በጄ የሚሉ አይሆኑም። እኛ የቀረን አንድ መንገድ በማንኛውም መንገድ አገራችንን ከጥፋት ማዳን ብቻ ነው። ይህም ታሪካዊ ግዴታችን ሁኗል።

ይህን አገርን የማዳን ታሪካዊ ግዴታ የዚህ ቡድን ወይም ደግሞ የዚያ አካል ብቻ ተደርጎ መወሰድ ያለበት ተግባር አይደለም። እያንዳንዱ ማሰብ የሚችል እና ለራሱ ትንሽ ክብር ያለው ዜጋ ሁሉ ኢትዮጵያን ለመታደግ የሚችለውን ጠጠር መወረወር ይጠበቅበታል። ኢትዮጵያ ሬድዋን ሁሴንን በመሳሰሉ ምናምንቴዎች ስትዋረድ እጅን አጣምሮ ቁሞ መታዘብ ትክክለኛ ተግባር አይሆንም። የአገሪቷ ድሃ ዜጎች ስቃያቸው በዝቶ እና ጭንቀታቸው ልክ አጥቶ እያየን ዝም ብንል እርግማን ይሁንብን ካሉ ዜጎች ጋር መተባበሪያ ግዜው አሁን ነው።

እኛ አርበኞች-ግንቦት ሰባት ለአንድነትና ለፍትህ ንቅናቄ አገራችን ከገባችበት የውርደት አዘቅት ውስጥ ለማውጣት የጀመርነውን ትግል እለት እለት እያደስነው፤ እለት እለት እያሰፋነው፤ እለት እለት እያሳደግነው ቀጥለናል። እኛ ዓይናችን እያየ ህዝባችን አይዋረድም፤ አገራችንም ከሥፍራዋ በታች ስትሆን ዝም አንልም።የሚከፈለውን ማንኛውንም መሥዋዕትነት ለመክፍለ አናቅማም። በአያት ቅደመ አያቶቻችን ደም ተከብራ የኖረች አገር ዳግም በእኛ ደም ተከብራ ትኖራለች። ቀጣዩ ትውልድም የተከበረች አገር ተርክቦ፤ እርሱም ተከብሮ ይኖር ዘንድ እኛ እንሰራለን እግዚአብሄርም ያከናውንልናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!**

..........................................................................................................

## ሐመር ዉስጥ ገበሬዎች እራሳቸዉን ለመከላከል በወሰዱት እርምጃ የወያኔን ፖሊሶች ገደሉ

ባሳለፍነዉ ሳምንት የኦሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ባወጣው መግለጫ እንዳመለከተው፤ ሐመሮች እራሳቸዉን ለመከላከል በወሰዱት የመልስ ማጥቃት እርምጃ የዞኑን የፖሊስ አዛዥ ሻምበል ለማ አሽናፊን ጨምሮ ሰባት ፖሊሶች ሲገደሉ፤ ስድስት ፖሊሶች ደግሞ ቁስለኛ ሆነዋል። በአሁኑ ወቅት ግጭቱ በተፈጠረበት አካባቢ የሚገኙ ፖሊሶች ልብሳቸውን በመቀየር በእግራቸው ወደ ጅንካ ከተማ እየሸሹ መሆኑን የአይን ምስክሮች ተናግረዋል።

ከፖሊሶቹ በተጨማሪ ሁለት ሲቪሎችም መገደላቸውና ሌሎች ሦስት ሰዎች ደግሞ መቁሰላቸው የፖሊስ ሪፖርት ያመለክታል። ፖሊሶችና የዞን መስተዳድር ሰራተኞች ከሐመር አርብቶ አደሮች ይህን ያህል ጥቃት የደረሰባቸው፤ በማጎ ፓርክ ውስጥ "የዱር አራዊት ገድላችሁዋል" ባሏቸው ወጣቶች ላይ የሀይል እርምጃ በመውሰዳቸው ነው። እንደ ፖሊስ ወቅታዊ የግጭት ሪፖርት ፣ ጥር 7/2007 ሐሙስ ዕለት በሐመር ወረዳ በ"ላላ" ቀበሌ በሐመር ብሔረሰብ አርብቶ አደሮችና ፖሊስ መካከል በተፈጠረ ግጭት የተገደሉት፤ የዞኑ ፖሊስ አዛዥ ሻምበል ለማ አሽናፊ፣ ወታደር ሙሴ ማቱሳላ፣ ወታደር ደፋሩ ጦና፣ ወታደር ካሪ፣ ወታደር በኃይሉ፣ ስሙ ለግዜዉ ያልታወቀ የልዩ ኃይል ባልደረባ፣ስሟ ለጊዜዉ ያልታወቀ ሴት ባለሙያ እናነመምህር መሳይነሽ መርነህ ናቸው።

ከሟቾቹ በተጨማሪ የደቡብ ኦሞ ዞን ፍትህ ጸጥታና ደንብ ማስከበር ምክትል ሀላፊአቶ ቹሜሬ የረር፣ ምክትል ሣጅን ጌታሁን ቶላ፣ወታደር ተሰማ መሰረት፣ ወታደር ጌታቸዉ ጸንቃ፣ ወታደር ቱላ ኪያ፣ ባሻ ወንድማገኝ ጨነቀ፣ ወታደር ሚልኪያስ ግራኝ፣ወታደር ዘለቀ እና የዞኑ ሴቶችና ሕጻናት መምርያ ሾፌር አቶ ደምሳሽ ሞላ ቆስለው ህክምና እየተከታተሉ ይገኛሉ። በአርብቶ አደሩ በኩል ስለደረሰው ጉዳት እስካሁን መረጃ ለማግኘት አልተቻለም። አስቀድመው ፖሊሶች እርምጃ እንዲወስዱ ዲመካ ሁነዉ ትእዛዝ ያስተላለፉትና ኦፐሬሽኑን ሲመሩ የነበሩት የሐመር ወረዳ ፍትህ ጸጥታና ደንብ ማስከበር ሃላፊ ኮማንደር ቡራ ካሎ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። ከዞኑ መስተዳድር የወጣ መረጃ እንደሚያመለከተው፤ በነገው ዕለት የዞኑ ሲቪል ሠራተኞች ከስከሬን አንሺ የቀን ሠራተኞችን ወደ ቦታው ይዘው በመሄድ አስከሬኖችን ለማምጣት የሚንቀሳቀሱ ሲሆን፤ በዚህ ጉዞ ወታደራዊ ኃይል እንዳይኖር ወይም እንዳያጅባቸው ተወስኗል።

በአሁኑ ሰዓት በሃመር ወረዳ ዋና ከተማ ዲመካ ምንም የፖሊስ ኃይል የሌለ ሲሆን፤ አንዳንድ የወረዳውና ከዞኑ የተንቀሳቀሱ ፖሊሶች የፖሊስ ልብሳቸውን በመቀየር በእግር ጫካ ለጫካ በመጓዝ ወደ ዞኑ ከተማ ወደ ጂንካ እያቀኑ ሲሆን፤ በሽሽት ነፍሳቸውን ያተረፉት ፖሊሶችም የጂንካ ከተማ ነዋሪ "እንኳን ለቤታችሁ አበቃችሁ" እያለ እየተቀበላቸው ነው። ፖሊሶቹም "በማናውቀው ነገር አስገብተውን ሊያስጨርሱን ነበር፣ የተፈጠረው ሁኔታ እና በወንድሞቻችን ላይ የደረሰው በእጅጉ አሳዛኝ ነው" በማለት ቁጭታቸውን እየገለጹ ይገኛሉ ።

የግጭቱን ምክንያቶች በዝርዝር ያስቀመጠው የኦሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት፤ መንግስት በግጭቱ ስለደረሰው አጠቃላይ ጉዳት በቂ መረጃ እንዲሠጥና በድርጊቱ አዛዦችና ፈጻሚዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ፤ በግጭቱ ለተጎዱ ወገኖችና ለደረሰው የንብረት ውድመት ካሳ እንዲከፍል፤ ግጭቱ ከመጪው ምርጫ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ስለሆነ አፋጣኝና አሳታፊ መፍትሄው እንዲፈልግለት፤ የፖሊስ ተግባራትና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ወደቦታቸው እንዲመለሱ እንዲያደርግ ጠይቋል። እንዲሁም ችግሩን ከስሩ ለማስወገድ ሕብረተሰቡን ያሳተፈና በማኅበረሰቡ ተቀባይነት ያለው አካባቢያዊ ዘላቂ መፍትሄ እንዲያበጅና ችግሩ እንዳይባባስና እንዳይስፋፋ አስቸኳይ የማረጋጋት እርምጃ እንዲወስድ የጠየቀው ድርጅቱ፤ የማንአለብኝነት የኃይል እርምጃ መቼውንም መፍትሄ አይሆንምና፤ ለቀጣይም መንግሥት ከዚህ ዓይነቱ አካሄድ እንዲታቀብ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን"ብሏል፡፡

## የመኢአድ ምክትል ፕሬዝደንት አዘዞ ጦር ካምፕ መወሰዳቸው ተነገረ

በፊት በፖሊሶች ከፍተኛ ድብደ ተፈጽሞባቸው ወዳልታወቀ ስፍራ ስለመወሰዳቸው የተዘገበው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ዘመነምህረት አዘዞ በሚገኘው መከላከያ ካምፕ መታየታቸውን ፓርቲያቸው ገለጸ። መኢአድ ዛሬ በሰጠው መግለጫ የድርጅቱ ምክትል ፕሬዝደንት እና የሰሜን ቀጠና ኃላፊ የሆኑት አቶ ዘመነ ምህረት የድርጅታቸውን ጠቅላላ ጉባኤ አድርገው ወደ መኖሪያቸው ጎንደር ከተማ ከተመለሱ በኋላ ከፍተኛ የደህንነት ክትትልና ጫና ይደረግባቸው እንደነበር ለፓርቲያቸው አሳውቀው እንደነበር አስታውሷል።

አቶ ዘመነ በ10/05/2007 ዓ.ም ጎንደር ከሚገኘው መኖሪያው ቤታቸው ከባቤታቸውና ከህጻን ልጃቸው ፊት የፖሊስ ልብስ በለበሱ አካላት ከፍተኛ ደብደባ ተፈጽሞባቸው ወዳልታወቀ ቦታ መወሰዳቸውን ያወሳው መኢአድ ፤በአሁኑ ወቅት የፓርቲው አባላት ባደረጉት ክትትል አዘዞ የሚገኘው የመከላከያ ካምፕ ውስጥ እንደሚኙ መረጋገጡን ገልጿል።

"በአቶ ዘመነ ላይ የደረሰባቸው ስቃይና እንግልት በሰው ልጅ ላይ ይፈጸማል ተብሎ ፈጽሞ የማይገመት ነው "ብሏል-መኢአድ። ከአቶ ዘመነ በተጨማሪ ጠቅላላ ጉባኤውን ተሳትፈው የተመለሱት የፓርቲው የማህበራዊ ጉዳይ ኃላፊ አቶ እያሱ ሁሴን 3 አመት ተፈርዶባቸው እስር ቤት እንደሚገኙ እንዲሁም የፓርቲው አመራር አካላት የሆኑት አቶ ተስፋዬ ታሪኩ፣ መቶ አለቃ ጌታቸው መኮንንና አቶ ጥላሁን አድማሴ ታስረው እየተሰቃዩ እንደሚገኙ ገልጿል።

በሌላ በኩል ምርጫ ቦርድ- መኢአድ በምርጫ 2007 እንዳይሳተፍ የኢህአዴግ ቀኝ እጅ ሆኖ በመስራት ላይ እንዳለ ያወሳው መግለጫው፤ ፓርቲው በምርጫው እንዳይሳተፍ ከተደረገ ሰላማዊ ትግሉን አጠናክሮ ይቀጥላል ብሏል። ምርጫ ቦርድና ኢህአዴግ በፓርቲው ላይ የሚፈጽሙትን በደል ለማስቆም በሚደርገው ትግልም ህዝቡ ከጎኑ እንዲቆም ጥሪ መኢአድ አቅርቧል።

ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል በሚገኙ የመኢአድ ፓርቲው አባላት ላይ ከፍተኛ ወከባና እስራት እየተፈጸመ መሆኑን ጠቅሶ፣ ይህ ጉዳይ የአገሪቱን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ሰላማዊ ትግል ክፉኛ የሚጎዳ በመሆኑ የፓርቲው አመራሮች እንዲፈቱ በጥብቅ አሳስቧል። ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር ፓርቲው ስለገባበት ውዝግብም በመግለጫው የተነሳ ሌላኛው ጉዳይ ሲሆን፣ "ቦርዱ በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ያልተገባ አካሄዱን እንዲያስተካክል አጥብቀን እንጠይቃለን" በማለት ጥያቄውን ለቦርዱም አቅርቧል።

የቦርዱን ያልተገባ ያለውን አካሄድ ከመተቸቱም በተጨማሪ፣ "የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ቦርድ አማካይነት በሚደረገው ጫና ከሰላማዊ ትግል ወደኋላ እንደማንል ቦርዱ ልብ ሊለው ይገባል፤" ካለ በኋላ፣ "የቦርዱን ጫና ተቋቁመን መቀጠል እንችላለን፤" በማለት ያለውን ዝግጁነት ገልጿል።

ጥር 5 ቀን 2007 ዓ.ም. በቦርዱ በተሰጠ ትዕዛዝ መሠረት ፓርቲው የውስጥ ችግሩን በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመፍታት፣ ከፓርቲው በልዩነት ከወጡ አባላት ጋር አንድ ላይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ ማዘዙ ይታወሳል። ይህን የቦርዱን ውሳኔ የተቃወመው መኢአድ፣ "ቦርዱ በመኢአድ ላይ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት ካላቆመ እስከ መጨረሻው ድረስ አስፈላጊውን መስዋዕትነት በመክፈል፣ በሰላማዊ መንገድ የምንቋቋመው መሆናችንን ለመላው ሕዝብ እንገልጻለን፤" በማለት የቦርዱን የተፅዕኖ ውሳኔ ለመወጣት ዝግጁነቱን ገልጿል።

## "ቃሊቲ ውስጥ የታሰሩ ንጹኋን ዜጎች ስቃይ አሁንም ከፊቴ አሉ" ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሺብዬ በኢትዮጵያ እየተፈጸመ ያለው የሰብዓዊ መብት ጥሰትና ግፍ ከሙያው አስገዳጅነት በመነሣት ከተባባሪዎቹ ጋር በመሆን ለዓለም እንደሚያሳውቅ ግልጽ አድርጓል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የፋሽስቱ ወያኔ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ለ 3 ኛ ጊዜ ይዞ በቀረበበት የተቆራረጠ ቪዲዮ ላይ በእስረኞች አያያዝ "ጻድቀ ጻድቃን" ነኝ ባለ 24 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የኖርዌይ ቴሌቪዥን Nrk2 (ኤንአርኮ 2) ያሰራጨው በኦጋዴን የተፈጸመውን ርኅራኄ የሌለውን ዘግናኝ ሰቆቃ የሚያሳይ ዘጋቢ ፊልም የወያኔን አውሬነት ያሳየ መሆኑ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አስተያየቶች እየተሰጡ ቀጥለዋል። በፋሽስቱ ወያኔ ፖሊስ ፕሮግራም የቀረበውን ዶክመንታሪ በተመለከተ አስተያየቱን የተጠየቀው ሺብየ ሲመልስ ዶክመንታሪው ድርሰትና በውሸት የታጨቀ መሆኑን በመጠቀም ፋሽስቱ ወያኔ ይህንን ያህል ከሚለፋ) ማዕከላዊን እና ቃሊቲን ለጋዜጠኞች፣ ለቀይ መስቀልና ለዓለምአቀፍ ተቋማት ክፍት በማድረግ ምስክር ማግኘት ብቻ ይበቃዋል ሲል ፕሮፓጋንዳውን አጣጥሎታል።

### የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ፡- በ 358 MB, በ 837 kHz

አጭር ሞገድ፡- በ 31 MB በ 9700 KHz

በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz

በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ለአድማ ብተና የሚሰጠዉን ስልጠና የተቃወሙ የፌዴራል ፖሊስ አባላት እርምጃ ተወሰደባቸዉ

የፌዴራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር የተባረሩት አብዮታዊ ዲሞክራሲን መቀበል ያልቻሉ ናቸው ብለዋል። በአሁኑ ወቅት በመላ ሀገሪቱ ፖሊሶችና ሚሊሻዎች ከምርጫው ጋር በተያያዘ ሊነሱ ይችላሉ የተባሉ ህዝባዊ አመጾችን ለማክሸፍ ያስችላል የተባለ የተኩስ ልምምድ እያደረጉ እንደሚገኙ ከየክልሎቹ የመጡ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከፍተኛ በጀት ተመድቦለት በፌድራል ፖሊስ አድማ ብተና አደረጃጀት በየክልሉ የሚካሄደውን ይህን ስልጠና " የፖሊስን ተልእኮና ዓላማ የሳተ ነው" በማለት በርካታ የፌዴራል ፖሊስ አባላት እንደተቃወሙት በፌዴራል ፖሊስ ውስጥ ያሉ የኢሳት ምንጮች ጠቁመዋል። ተቃውሞ ካነሱት መካከል 206 የፌዴራል ፖሊስ አባላት ተገምግምው ከስልጠናው እንዲወገዱ መደረጋቸውን ምንጮቻችን ገልጸዋል። ከነዚህ መካከል በ97ቱ ላይ እርምጃ ሲወሰድ፤ 119ኙ እስከ ምርጫው መጠናቀቅ ድረስ የግዳጅ እረፍት እንዲወጡ ተደርጓል።

የፌዴራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ጄነራል አቶ አሰፋ በዩ እርምጃ የተወሰደባቸውንና የግዳጅ እረፍት እንዲወጡ የተደረጉትን የፌዴራል ፖሊስ አባላት አስመልክተው ለኢህአዴግ የምርጫ ጊዚያዊ ኮሚቴ በላኩት ደብዳቤ ፡-"አብዮታዊ ዲሞክራሲን መቀበል ያልቻሉ ናቸው" ማለታቸውም ተመልክቷል። በመሆኑም በምርጫው ደህንነት ጥበቃ ላይ እንዳይሳተፉ መታገዳቸውን ዳይሬክተሩ በደብዳቤያቸው ገልጸዋል።

ምንጮቻችን እንደሚሉት ግን "አብዮታዊ ዲሞክራሲን መቀበል ያልቻሉ" በሚል ምክንያት ከስራቸው እንዲታገዱም ሆነ በግዳጅ እረፍት እንዲወጡ የተደረጉት በብሄራቸው እየተመረጡ "ለስርዓቱ ታማኝ አይደሉም፣ ግርግር ከተነሳ ሊከዱን ይችላሉ"ተብለው የተጠረጠሩ ፖሊሶች ናቸው። ይህ በእንዲ እንዳለ በአማራ ክልል በከፍተኛ የስራ እርከን ላይ የሚገኙ የስራ ሂደት ሃላፊዎችና ካድሬዎች ትናንት ሀሙስ እና እና ዛሬ በምርጫው ዙሪያ ስብሰባ ማድረጋቸውን ከስፍራው የደረሰን ዜና ያመለክታል።

## ወያኔ የይስሙላ ምርጫዉን ለሚያዳምቁለት አጋራቹ 200. 4 ሚሊዩን ብር ድጎማ አደረገ

የማይፈልጋቸዉን ፓርቲዎች እየጨፈለቀ የራሱን ተለጣፊ ፓርቲ በመፍጠር የሚታወቀዉ ወያኔ መኢአድንና አንድነት ፓርቲን ከጨወታ ዉጭ ካደረገ በኋላ ዬኔ ለሚላቸዉና በብሄር ስብስቦ ላደራጃቸዉ ፓርቲዎች የገንዝብ ድጎማ ማድረጉ ተሰማ። የገንዝብ ድጎማ ከተደረገላቸዉ ፓርቲዎች የተገኘ መረጃ እንደሚጠቁመዉ በመጀመሪያው ዙር ፈሰስ የተደረገው ይህ ገንዘብ ለቲሸርት ፤ ለኮፍያ፤ እና ለበራሪ ወረቀቶች ህትመት የሚውል ነው ተብሏል። ለፕሮሞሺን ስራ አገልግሎት የሚውል ተብሎ በብሄር ለተደራጁ ድርጅቶች ፈሰስ ከተደረገው ከዚህ ገንዘብ ባሻገር ለአራቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች ማለትም ለህወሀት፣ ለብአዴን፣ ለኦህዴድ እና ለደኢህዴግ 5 ሚሊዮን 87 ሺህ 307 ብር ከ75 ሳንቲም በየአካውንታቸው ገቢ መደረጉን ምንጮቹ አመልክተዋል።

ኢህአዴግ ላባል ድርጅቶቹ ያከፋፈለውን ይህን ገንዘብ "ከአባላት ክፍያ ያሰባሰብኩት ነው" ማለቱም ተሰምቷል። ኢህአዴግ ከዚህም በላይ ከግንቦቱ ምርጫ ጋር በተያያዘ ከበለሃብቱ ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ለማሰባሰብ እቅድ ማውጣቱና ይህንንም እቅዱን በዚሁ በጥር ወር አጋማሺ ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ መሆኑ ታውቋል። የሚሰበሰበው ገንዘብ በኢህአዴግ ግምገማ" የምርጫው የስጋት ቀጠናዎች "ተብለው በተለዩት በአማራ፤ ኦሮምያ፤ ትግራይ እና ደቡብ ክልሎች ድጋፍን ለማጠናከር ይውላል መባሉንም የምንጮቻችን መረጃ ያመለክታል።

## ከፍተኛዎቹ የወያኔ ባለስልጣናት ድግሪ የተሸከሙት በጥቂት ቀናት ትምህርት መሆኑን ምንጮች አጋለጡ

ሀገሪቱ የምትመራበትን ፖሊሲ ከመጠምዘዝ ጀምሮ ድርጊቱ በሀገርና በህዝብ ላይ የከፋ ተጽእኖ እንዳለው የተገነዘቡ ኢትዮጲያውያን በዩኒቨርሲቲው ላይ የተቃውሞ ዘመቻ እያስተባበሩ ነው። አዲስ አበባ የሚገኘው ኢንተርናሽናል ሊደር ሺፕ ኢንስቲትዩት አማካይነት የሚቀርቡለትን ባለስልጣናት በአጭር ቀናት ኮርስ በማስተርስ ዲግሪ እያንሸበሸ ያለው፤ በእንግሊዝ ሀገር የሚገኘው የግሪንዊች ዩኒቨርሲቲ ነው። በአይ ኤል አይ ድረገጽ እንደተመለከተው ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝን ጨምሮ ሁሉም የሀገሪቱ ባለስልጣናት በቀናት ኮርስ ከአንድ ትምህርት ቤት ማለትም ከግሪንዊች ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ዲግሪ እንዲወስዱ ተደርገዋል።

እነሱም፡-አፈ-ጉባኤ አባዱላ ገመዳ፣ የቀድሞው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አዲሱ ለገሰ፣የቀድሞው የኮሙኒኬሽን ሚኒስትርና የ አሁኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የፖሊሲ አማካሪ በረከት ስምኦን፣ የሱማሌ ክልል ፕሬዚዳንት አብዲ መሀመድ ኡመር፣ የቀድሞው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር ጁነዲን ሳዶ፣ የቀድሞው የ አዲስ አበባ ከንቲባ አቶ ኩማ ደመቅሳ፣ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ሙክታር ከድር፣ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ዶኤታ ሽፈራው ተክለማርያም፤ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትር ሬድዋን ሁሴን፣ የትምርት ሚኒስትር ሽፈራው ሽጉጤ፣ የሲቪል ሰርቪስ ምክትል ሚኒስትር አስቴር ማሞ፣ የቀድሞው መከላከያ ሚኒስትርና የ አሁኑ የ አዲስ አበባ ከንቲባ ድሪባ ኩማ፣ የሴቶች፣ የህጻናትና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስትር ዘነቡ ታደሰ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ ካሳ ተክለብርሀን፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ደሴ ዳልክዬ ዱካሞ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ዶኤታ አብርሐም ተከስተመስቀል፣ የቀድሞ መከላከያ ሚኒስተርር ሲራጅ ፈርጌሳ፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዶኤታ ዳውድ መሀመድ አሊ፣የትራንስፖርት ሚኒስትር ዶኤታ ተከስተ ረባ አያና፣በፌዴሬሽን ምክር ቤት የትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሙፈሪያት ካሚል አህመድ እና በመከላከያ ሚኒስትር የምእራብ እዝ አዛዥ ሜጀር ጀነራል ብርሀኑ ጁላ ጋላቻ ናቸው።

በኢንተርናሽናል ሊደር ሽፕ ኢንስቲትዩት ድረ-ገጽ ከተዘረዘሩት ከነኘህ ባለስልጣናት ባሻገር የሀገሪቱ ጀነራሎችና የጦር አዛዦች እንዲሆም የየዞኑ የቢሮ ሀላፊዎች በሙሉ በሶስትና አራት ቀናት ኮርስ ከዚሁ ከግሪንዎች ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ዲግሪ መያዛቸውን በአንድ ወቅት በዩኒቨርሲቲው መምህር የነበሩት ዶክተር ታደሰ ብሩ ይናገራሉ።

የማስተርስ ዲግሪ ከወሰዱት ከነኘህ ሹመኞች መካከል በጣት የሚቆጠሩ ጥቂቶች በራሳቸው የተማሩ ቢሆንም፤ በርካታዎቹ የ2ለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚገባ ስለማጠናቀቃቸው ትክክለኛ ማረጋገጫ ማቅረብ አይቻልም። ከጠቅላይ ሚኒስትሩና ከትምህርት ሚኒስትሩ ጀምሮ አሉ ለሚባሉ የሐገሪቱ ሹማምንት ሁሉ የማስተርስ ዲግሪ በዚህ መልክ መታደሉ በሀገሪቱ ፖሊሲዎችና የወደፊት አቅጣጫዎች ላይ ያለው ተጽ እኖ ከፍተኛ እንደሆነ ዶክተር ታደሰ ያብራራሉ።

የግሪንዊች ዩኒቨርሲቲንም "ሀገሪቱን እጅ የጠመዘዘ፣ ሀገሪቱን እኪሱ ያስገባ ተቋም" ብለውታል ዶክተር ታደሰ። የትምህርት ሚኒስትሩ ዕፈራው ሽጉጤ ከዚሁ ከግሪንዊች ተቋም መመረቃቸው የሚፈጥረን የጥቅም ግጭት ዶክተር ታደሰ ሲያብራሩም ይህ ድርጊት ለዩኒቨርሲቲውም እፍረት ነው፤ ለሀገራችንም ጉዳት ነው ያሉት ዶክተር ታደሰ፤ የዩኒቨርሲቲውን ድርጊት ለመቃወም ፒቲሺን ፈርሞ የማስገባት እንቅስቃሴ መጀመሩን በማውሳት፤ ኢትዮጲያውያን በተቃውሞ ዘመቻው እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል።

## ህወሓት በምርጫ ቦርድ አማካይነት አንድነት ፓርቲን ለማፍረስ የጠነሰሰው ሴራ ተጋለጠ

ኢህአዴግና ምርጫ ቦርድ አንድነት ፓርቲ ለሁለት እንደተሰነጠቀ በማስመሰል ያቀነባበሩት ሴራ መጋለጡን እና መክሸፉን ከፓርቲው ጽሕፈት ቤት የደረሰን ዜና ያመለክታል። ምርጫ ቦርድ "የአንድነትን ጠቅላላ ጉባኤ ጠርተዋል" ሲላቸው የነበሩት አቶ አየለ ስሜነህ፤ በዛሬው እለት "አንድነት አንድ ነው፤ እናት ፓርቲዬን ለማዳን ተመልሻለሁ" በማለት በአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት መግለጫ ሰጥተዋል።በአንድነት ስም ተጠራ የተባለውን የዲ-አፍሪኩን ስብሰባም እነሱ እንዳልጠሩትና ህገ-ወጥ ነው ብለው እንደሚያምኑ አቶ አየለ ተናግረዋል።

የአንድነት ፓርቲ የሚዲያ ክፍል፤ ህወሃት/ኢህአዴግ፣ ምርጫ ቦርድ፣ ራዲዮ ፋና እና በቅርቡ ኢቢሲ የተባለው የቀድሞው ኢቲቪ ተቀናጅተው ሲሰሩ የሰነበሩትን ፕሮፖጋንዳ የሚያጋልጥ ዘጋቢ ፊልም ይፋ እንደሚያደርግም አስታውቋል።ዘግይቶ በደረሰን መረጃ መሰረት "ወደ ቤቴ ተመልሻለሁ" ወደ እናት ፓርቲያቸው የተመለሱት እና የ ኢህአዴግን እና የምርጫ ቦርድን ሴራ ያከሸፉት አቶ አየለ ስሜነህ ከደህንነቶች ማስፈራሪያና ዛቻ እየተሰነዘረባቸው ነው።" አንድነት ኖረም አልኖረም፣ ይሄ ትግል ጥርጥር በሌለው ሁኔታ ይቀጥላል" ሲሉ አቶ በላይ ፈቃዱ ገልጹ። የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ሊቀመንበር አቶ በላይ ፈቃዱ ከድርጅታቸው ልሳን ከፍኖተ-ነጻነት ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ፤ ፓርቲያቸው ወደነጻነት ትግል የሚያመራ ከመሆኑ አንጻር ምርጫ ቦርድ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ፓርቲውን ለመዝጋት መነሳቱ፤ ትግሉን አንድ እርከን ከፍ እንደሚያደርገው ተናግረዋል። "ትግሉ ከርዕዮተ-ዓለም የዘለለ የነፃነት ትግል ነው፤ይህ ማለት ትግሉ የግድ ስልጣን መጨበጫ ብቻ ሳይሆን፤ ነፃ እና ገለልተኛ የዴሞክራሲ ተቋማት መፍጠሪያ ይሆናል ማለት ነው።" ያሉት ሊቀመንበሩ፤" ስለዚህ አንድነት ኖረም አልኖረም፣ ይሄ ትግል ጥርጥር በሌለው ሁኔታ ይቀጥላል።"ብለዋል። አቶ በላይ አክለውም "አሁን ሌላ አቋም ላይ ደርሰናል፤ እንዲህ አይነት "ምርጫ ቦርድ" ባለበት ሀገር የፓርቲ ፖለቲካ እንደማያዋጣ አቋም ይዘናል።" ብለዋል።

ፓርቲ፣ ለስልጣን የሚታገል ኃይል ነው ቢባልም መሠረታዊ የዴሞክራሲ ተቋማት በሌሉበት በፓርቲ ደረጃ ያንን ማሰብ እንደማይቻል ያስረዱት ሊቀመንበሩ፤ "እዚህ ሀገር መደራጀት አትችልም፤ በራሪ ወረቀት መበተን አይቻልም፤ የደህንነት ክትትሉ ልብህን ያወልቃል። ይህ ከሆነ በፓርቲ ፖለቲካ ስልጣን መያዝ ይቻላል የሚለውን እምነት መልሰን መላልሰን መጠየቅ አለብን።" ብለዋል።" ጥያቄው የነፃነት ትግሉ እንዴት ይፋፋም? የሚል ነው ያሉት አቶ በላይ፤ "በመላ ሀገሪቱ ወደ 40 የሚጠጉ ቢሮዎች አሉን፤ ለነፃነት ትግሉ ድጋፍ መስጠት የሚፈልግ የትኛውም አካል ቢሮውን መጋራት ይችላል። ይህን አቋም የያዝነው ነውጥ-አልባ ትግል፤ብቸኛው የነፃነት መንገድ ነው የሚለውን በሰፊ ጥሞና ስለደረስንበት ነው።" ብለዋል። "ከምርጫ ቦርድ ጋር የገባንበትን ጭቅጭቅ እንደ ትልቅ ዕድልም፣ ድልም አድርገን የምናየው የድሉ መንገድ ይህ ስለሆነ ነው" ብለዋል የአንድነት ሊቀመንበር።

ከምርጫ ቦርድ ጋር በመግባባት ለመስራት በርካታ ጥረቶች ቢደረጉም ቦርዱ ፖለቲካዊ አቋም በመያዙ ሊሳካ አለመቻሉን ያወሱት ሊቀመንበሩ፤ "ስርዓቱ፣ ለአፈና በቢሊየን የሚቆጠር ዶላር ፈሰስ እያደረገ ባለበት ሁኔታ ያለው አማራጭ ህዝባዊ ንቅናቄ ማድረግ እንደሆነና ይህንንም ለማሳካት ከሌሎች የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር መተባበር የግድ እንደሆነ አስምረውበታል።